# ቤት መባረሪያ ማሳሰቢያን አያያዝ

## ያለስምምነት ማቋረጥ/ከቤት መባረር

### ከቤት መባረር ባጠቃላይ

- ከቤት መባረር ማለት አንድ ተከራይ መኖሪያውን እንዲለቅ በፍርድ ቤት ሲታዘዝ ነው። ይህንን የፍርድ ቤት ትእዛዝ ማስፈጸም የሚችለው የፖሊስ መኮንን ብቻ ሲሆን፥ አከራዮች ያለፍርድ ቤት ትእዛዝና ያለ ፖሊስ መኮንን ማባረር አይችሉም። ልብ ይበሉ፦ በዴንቨር ውስጥ ከቤት መባረርን የሚተገብሩት ምክትል ፖሊስ መኮንኖች ናቸው። ይህ ዓይነት ሕጋዊ እርምጃ Forcible Entry and Detainer (FED) (የግዳጅ መግቢያና መያዣ)።
- አከራዮች ያለፍርድ ቤት ትእዛዝ ተከራዮች መኖሪያቸው ውስጥ እንዳይገቡ መከልከል፥ የበር ቁልፍ መቀየር ወይም የተከራዮችን ንብረት ማስወገድ አይችሉም።
- ተከራዩ ኪራይ ካልከፈለ ወይም የኪራዩን ውል ከጣሰ፥ የ FED ሂደት ለመጀመር የቀረውን የኪራይ ሒሳብ የሚጠቅስ ወይም የተጣሰውን የኪራይ ውል የሚገልጽ የTen-Day Demand for Compliance or Possession (Ten-Day Demand) (በአሥር ቀናት ውስጥ የመስማማት ጥያቄ ወይም ውርስ (የአሥር ቀናት ጥያቄ)) አከራይ ለተከራይ መስጠት አለበት። ተከራዩ በአሥር ቀን ውስጥ ቀሪ ኪራይ ካለበት ሒሳቡን መክፈል፥ የተጣሰውን ውል ማስተካከል፥ መውጣት ወይም በፍርድ ቤት ውስጥ ዳኛ ፊት ቀርቦ የመባረር ትእዛዙን መከራከር ይችላል። አይደለም ካለ ትክክሉን ሒሳብ በአሥር ቀናት ውስጥ መክፈል አለበት። የአሥር ቀን ወቅቱ ካለፈ በኋላ አከራዩ ክፍያ የመቀበል ግዴታ **የለበትም።**
- አከራዩ የTen-Day Demandዱን በቀጥታ ለተከራይ ለማቅረብ ሞክሮ ካቃተው ግልባጩን በተከራዩ መኖሪያ ቦታ ውስጥ ላለ ዕድሜው አሥራ ስምንት ዓመት ወይም ከዛ በላይ ለሆነ ለማንኛውም የቤተሰብ አባል መስጠት ወይም የግለሰቡ መሥሪያ ቤት ውስጥ ለግለሰቡ አለቃ፥ ጸሐፊ፥ ረዳት፥ ሒሳብ ያዥ፥ የሰው ኃይል ተወካይ ወይም አስተዳዳሪ ወኪል መስጠት፥ ወይም መኖሪያ ቦታው ላይ በግልጽ የሚታይ ቦታ ላይ ማለትም መግቢያ በር ላይ መለጠፍ ይችላል። ተከራዩ ማስታወቂያውን ቢያይም ባያይም አሥር ቀኖቹ መቆጠር የሚጀምሩት ማስታወቂያው በደረሰ ወይም በተለጠፈ በማግስቱ ነው።

> **የተከራይ ጠቃሚ ምክሮች**
>
> ከአከራይዎ የTen-Day Notice እንደደረሰዎት፥ ወዲያውኑ Office of Financial Empowerment and Protectionንን በስልክ ቁጥር 720-944-2498 ወይም በFEC@denvergov.org ኢሜል በማድረግ ይገናኙ። ከአሰሳ ረዳት ጋር ያገናኙዎትና ወደሚከተሉት ይመራዎታል፦
>
> - የኪራይ እርዳታ
> - ሕጋዊ አገልግሎቶች
> - የሽምግልና አገልግሎቶች
> - በክልሉ መንግሥት ድርጅቶችና ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶች አማካኝነት ሌሎች አገልግሎቶች

- ተከራዩ ካልከፈለ፥ የውል ጥሰቱን ካላረመ ወይም ከመኖሪያው ካልወጣ አከራዩ ከቤት ማስወጫ ክስ ማስገባት ይችላል። የዚህ ሂደት ዝርዝር ደረጃዎች ተያይዞ የሚገኘው Denver Eviction Process Chart (የዴንቨር ማባረሪያ ሂደት ሠንጠረዥ) ውስጥ ይገኛሉ።
- የTen-Day Demand መስፈርቶች ሁልጊዜም ይተገበራሉ፥ የውሉ ስምምነት ላይ ሌላ ነገር ተጽፎ ቢሆንም።

### ከቤት የመባረር ሂደት

- የTen-Day Demand ተሰጥቶ ተከራዩ በክሶቹ ካልተስማማ፥ ችግሩን ለመፍታት ተከራዩ አከራዩን፥ የColorado Legal Services (የኮሎራዶ ሕጋዊ አገልግሎቶች) (coloradolegalservices.org፥ 303-837-1313)ን ወይም Community Mediation Concepts (የማህበረሰብ ሽምግልና ጽንሰ ሐሳቦች) (CMC@FindSolutions.org፥ 303-717-4151)ን መገናኘት ይችላል። ይበልጥ ዝርዝር ለማግኘት የአገልግሎቶች ክፍሉን ይመልከቱ።
- የማባረር ክስ ሲመዘገብ፥ አከራዩ የቅሬታውንና የመጥሪያ ግልባጩን ለተከራይ መስጠት አለበት። መጥሪያው ተከራዩ በምን ቀንና ሰዓት ፍርድ ቤት መቅረብ እንዳለበት ይናገራል። የ Denver County Court (የዴንቨር አውራጃ ፍርድ ቤት) በሩቁ እንዴት መገናኘት እንደሚቻል የሚገልጽ መመሪያ ከመጥሪያው ጋር መቅረብ አለበት።

  በቀጠሮው ቀን ተከራዩ መልስ ማስገባት ወይም አከራዩ በዛ ዕለት ለፍርድ ቤት ሊያስገባው የሚችል የጽሑፍ ስምምነት ላይ መድረስ አለበት። ተከራዩ ከሁለቱ አንዱን ካላደረገ የንብረት ውርስ ነባሪ ፍርድ (የማባረር ፍርድ) ይፈረድበታል።

- ተከራዩ ምላሽ ማስገባት ፈልጎ ወጪውን የማይችለው ከሆነ (በግምት $100)፥ የፍርድ ቤት ጸሐፊው ያለክፍያ መልስ ማስገቢያ ቅጽ እንዲሰጠው መጠየቅ ይችላል።

- ተከራዩ መልስ ካስገባ የችሎት ቀጠሮ ቀን በሰባት (7) ቀን ውስጥ ይያዛል።

- የማባረሪያ ትእዛዝ ከፍርድ ቤት ከተገኘ፥ አከራዩ ማስወጣቱን የሚከታተል ምክትል ፖሊስ መኮንን መገናኘት አለበት። በስቴቱ ሕግ መሠረት፥ ውሉ የሚፈቅድ ከሆነ የመባረር ክስ አሸናፊው አግባብ ያለው የጠበቃ ክፍያ ዋጋውን ከሌላው ወገን ማስመለስ ይችላል።

- አከራዮች ያለ ፍርድ ቤት ትእዛዝና ያለ ምክትል ፖሊስ መኮንን ተከራዮችን ማስወጣት ወይም ተከራዩ ቤቱ እንዳይገባ መከለከል አይችሉም። ኃይል መጠቀም ወይም ማስፈራራት ለፖሊስ ሪፖርት መደረግ አለበት። ቤቱ ተቆልፎ ተከራዩ መግባት ካልቻለ ኃይል ተጠቅሞ ለመግባት ባይሞከር ይመረጣል፥ እንዲሁም ወዲያውኑ Colorado Legal Servicesን (የኮሎራዶ ሕጋዊ አገልግሎቶች) ወይም ጠበቃን ማማከር አለበት።

## የኪራይ ውል ስምምነትን በተደጋጋሚ ወይም በከፍተኛ መንገድ መጣስ

- Ten-Day Demand ከዚህ በፊት ተሰጥቶት ከነበረና አንድ ተከራይ የኪራይ ውሉን በተደጋጋሚ ቢጥስ ወይም ይበልጥ የከፉ መጣሶች ለምሳሌ ዓመጽና አደንዛዥ ዕጽ ቢኖሩ፥ አከራዩ “Notice to Quit” (ለማቆም ማስታወቂያ) መስጠት ወይም መለጠፍ ይችላል፥ ይህም ተከራዩ መጣሱን እንዲያርም ዕድል አይሰጥም። የከፋ መጣስ ሲሆን ተከራዩ በሶስት ቀን ውስጥ፥ ብዙ ጊዜ ለተደረገ መጣስ በአሥር ቀን ውስጥ መልቀቅ አለበት ወይም የመባረር ማሳሰቢያውን በፍርድ ቤት ውስጥ ዳኛ ፊት መከራከር ይችላል።

- አከራዮች ተከራይ በቤት ውስጥ ሕገወጥ አደንዛዥ ዕጾችን፥ የመዝናኛም ሆነ የሕክምና ማሪዋናን ጨምሮ እንዳይጠቀም መከልከል ይችላሉ።

- ባጠቃላይ፥ የቤት ውስጥ ጥቃት ተጎጂዎች በቤት ውስጥ ጥቃት ምክንያት ከቤት ሊባረሩ አይችሉም። በቤት ውስጥ ጥቃት ምክንያት ከቤት ውስጥ ለማስወጣት የፖሊስ መዝገብ ወይም የሰብዓዊ ጥበቃ ትእዛዝ ሊያስፈልግ ይችላል።

- አንድ አከራይ የኪራይ ውሉን አቋርጦ ተከራዩን ከማንኛውም ዓይነት መኖሪያ ማስወጣት የሚችለው የ Forced Entry and Detainer (FED) ሕጋዊ እርምጃ ወስዶ ተከራዩ ከመኖሪያው እንዲወጣ የፍርድ ቤት ትእዛዝ በማግኘት ነው። አከራይ ያለፍርድ ቤት ትእዛዝ ተከራይን ማባረር ሕገወጥ ነው።

- የNotice to Quit ወቅት ተከራዩ እንደቆየበት ጊዜና የኪራይ ውል ውስጥ እንደተሰጠው የማስታወቂያ ጊዜ ርዝመት 3 ቀናት፥ 21 ቀናት፥ 28 ቀናት ወይም 91 ቀናት ነው። (Colorado Revised Statute 13-40-107 (የኮሎራዶ የተሻሻለ ደንብ 13-40-107))

- ስደተኞችና ወረቀት አልባ ቤተሰቦች ከሌሎች የዴንቨር ነዋሪዎች ጋር ተመሳሳይ የተከራይ ጥበቃ መብቶች አሏቸው።

- አከራዩና ተከራይ ለፍርድ ከመቅረብ ይልቅ በግላቸው ስምምነት ላይ መድረስ ወይም ጉዳዩን መፍታት ይችላሉ።

- ተከራዩ በፍርድ ቤት ችሎቱ ላይ ቢሸነፍም፥ ምክትል ፖሊስ መኮንኑ ለማስወጣት ከመምጣቱ በፊት አከራዩና ተከራይ ስምምነት ላይ መድረስ ይችላሉ። ይህ ዓይነት ስምምነት በጽሑፍ መሆን አለበት።

# ከቤት መባረሪያዎች የጊዜ ሠንጠረዥ




የተከራይ እርምጃ

የአከራይ እርምጃ

**ድጋፍ ለማግኘትና ተገቢዎቹን አገልግሎቶች ለማግኘት Office of Financial Empowerment and Protection ጋር በስልክ ቁጥር **720-944-2498** ይደውሉ ወይም በ**FEC@denvergov.org**. ኢሜል ያድርጉ።

# ከቤት መባረርን ለተጋፈጡ የዴንቨር ነዋሪዎች አገልግሎቶች

| | |
|---|---|
| DENVER OFFICE OF FINANCIAL EMPOWERMENT AND PROTECTION, CONSUMER FINANCIAL PROTECTION UNIT(የገንዘብ ማጎልበትና ጥበቃ ቢሮ፥ የተጠቃሚዎች ገንዘብ ጥበቃ ክፍል)<br>• ግለሰቦችን፥ ቤተሰቦችንና አነስተኛ ንግዶችን የሚያገለግል<br>• የአሰሳ አገልግሎቶች<br>• አንድ ላንድ የሆነ ነጻ የሒሳብ ስልጠና<br>• የተጠቃሚ ገንዘብ ጥበቃ (የገንዘብ ማጭበርበርን መፍታትና ትክክለኛ የመኖሪያ አሠራሮችን ማስተዋወቅ)<br>• የዕዳ አያያዝ<br>• የክሬዲት ማረጋገጫዎች | 720-944-2498<br><br>ለገንዘብ ስልጠና FEC@denvergov.org ጋር ኢሜል ያድርጉ።<br><br>ለአሰሳ ወይም ለተጠቃሚ ገንዘብ ጥበቃ ድጋፍ cfpd@denvergov.org ጋር ኢሜል ያድርጉ። |
| DENVER DEPARTMENT OF HOUSING STABILITY (HOST) (የዴንቨር የተረጋጋ መኖሪያ መምሪያ)<br><br>HOST የዴንቨር ኗሪዎችን ለመርዳት የሚከተሉን አገልግሎቶች ያቀርባል፦<br>• አዲስ መኖሪያ ማግኘት<br>• ባሉበት መኖሪያ መቆየት<br>• መጠለያ ማግኘት<br>• ኪራይ፥ የመስመር ግልጋሎት ፍጆታና ሞርጌጅ መክፈል<br>• የሃራጅና የመባረር ሂደቶችን መረዳት<br>በተጨማሪም HOST የ **TEMPORARY RENT AND UTILITY ASSISTANCE (TRUA) (ጊዜያዊ የኪራይና የመስመር ግልጋሎት ፍጆታ እርዳታ)** ፕሮግራምን ያስተዳድራል።<br>ከDepartment of Housing Stability የሚገኝ የኪራይና የመስመር ግልጋሎት ፍጆታ እርዳታ የገንዘብ ችግር ያጋጠማቸው የዴንቨር ከተማና አውራጃ ኗሪዎች ከመኖሪያቸው እንዳይባረሩ ወይም የመስመር ግልጋሎት ፍጆታ እንዳይዘጋባቸው እርዳታ ያቀርባል። ኪራይ ወይም ፍጆታ ለመክፈል እርዳታ ካስፈለግዎት ጊዜያዊ ድጋፍ ለማግኘት ብቃት ሊኖርዎት ይችላል። | Denvergov.org/Housing<br><br>720-913-1534<br><br>housingstability@denvergov.org |
| DENVER HUMAN SERVICES **(የዴንቨር ሰብዓዊ አገልግሎቶች)**<br><br>Denver Human Services ብቁ ለሆኑ ቤታቸውን ለማጣት ለተጋለጡ የዴንቨር ነዋሪዎች የተቀማጭ ገንዘብ፥ የመጀመሪያ ወር ኪራይ ክፍያ፥ የሞርጌጅ፥ የቤት መባረር፥ የኪራይና የጥሬ ገንዘብ እርዳታን ጨምሮ የተለያዩ አገልግሎቶች ይሰጣል። Denver Human Services በሚከተሉት ጉዳዮች ላይም ለነዋሪዎች ድጋፍ ማድረግ ይችላል፦<br>• የባሕሪያዊ ጤና/የአእምሮ ጤና አገልግሎቶች<br>• በተለይ ዕድሜያቸው ለገፋ አዋቂዎችና ለአዛውንቶች አገልግሎቶች<br>• የምግብ አገልግሎቶች፥ Supplemental Nutrition Assistance Program (SNAP) (ተጨማሪ የምግብ ድጋፍ መርሃ ግብር) እና የምግብ ጓዳ ጥቆማን ጨምሮ<br>• ለወታደሮች/በውትድርና ላገለገሉ ሰዎችና ቤተሰቦቻቸው አገልግሎቶች<br>• ከሥራና ሥልጠና ጋር ግንኙነቶች<br>• Supplemental Security Income (SSI) (ተጨማሪ የደህንነት ገቢ)ን ማግኘት፥ የአካል ጉዳተኛ ለሆኑ አገልግሎቶች፥ መልሶ ማገገም ወይም የአደንዛዥ ዕጽ ሕክምና እንዲሁም ሌሎች | የምግብ፥ ጥሬ ገንዘብ፥ ሕክምናና የልጅ ጥበቃ ድጋፍ ለማግኘት በColorado.gov/PEAK ማመልከቻ ያስገቡ<br><br>ስለ ዴንቨር ሰብዓዊ አገልግሎቶች የድንገተኛ ጊዜ ድጋፍ መርሃ ግብሮች ይበልጥ መረጃ ለማግኘት Denvergov.org/HumanServices ይጎብኙ ወይም በ 720-944-2032 ይደውሉ።<br><br>ስለ ዴንቨር ሰብዓዊ አገልግሎቶች መርሃ ግብሮችና አገልግሎቶች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት በ 720-944-4DHS (4347) ይደውሉ። |
| **የዴንቨር አውራጃ ፍርድ ቤት**<br><br>የዴንቨር አውራጃ ፍርድ ቤት ስለ ፍርድ ቤት ሂደቶችና በኢንተርኔት የፍርድ ቤት ሂደት ላይ ስለመካፈል ለግለሰቦች መረጃና አገልግሎቶች ያቀርባል። | denvercountycourt.org/civil-matters-in-denver<br><br>courts.state.co.us/Courts/District/Custom.cfm?District_ID=2&Page_ID=856 |

| | |
|---|---|
| **LOW-INCOME ENERGY ASSISTANCE PROGRAM (LEAP) (ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው የመስመር ግልጋሎት ፍጆታ ድጋፍ መርሃ ግብር)**<br><br>LEAP የፌዴራል ገንዘብ ድጋፍ የሚደረግለት፥ ብቁ ሆነው ለተገኙ ቤቶች የቤት ማሞቂያ ሒሳባቸውን በከፊል በመክፈል እገዛ የሚያደርግ መርሃ ግብር ነው። ማመልከቻዎችን ለማስተናገድ 30 ቀናት ሊፈጅ የሚችል ሲሆን፥ የመዝጊያ ማስታወቂያ ለደረሳቸው ዓይነት አስቸኳይ ሁኔታዎች ግን ከዚህ በፈጠነ ሁኔታ ሊስተናገዱ ይችላሉ። ማመልከቻዎች ተቀባይነት ያላቸው ከኖቬምበር እስከ ኤፕሪል ነው።<br><br>ከቤት ማሞቂያ ጋር የተያያዘ ድንገተኛ ሁኔታ ካጋጠምዎት Energy Outreach Colorado (የኮሎራዶ ኃይል አቅርቦት) ሊረዳዎት ይችል ይሆናል። | የEnergy Outreach Colorado አካል የሆነው HEAT HELP (የቤት ማሞቂያ እርዳታ) መስመር ጋር በስልክ ቁጥር (በቀን 24 ሰዓት፥ በሳምንት 7 ቀን ማግኘት ይቻላል) at 866-431-8435 ይደውሉ።<br><br>**Denvergov.org/LEAP** |
| **COLORADO LEGAL SERVICES(የኮሎራዶ ሕግ-ነክ አገልግሎቶች)**<br><br>Colorado Legal Services (CLS) የተለያዩ የመኖሪያ መባረሮችን በተመለከተ የገቢ መስፈርት ለሚያሟሉ ግለሰቦችና ቤተሰቦች የነጻ ሕጋዊ አገልግሎቶች ያቀርባል። CLS ለአዛውንቶች ተመሳሳይ አገልግሎቶችን ገቢን ከግምት ሳያስገባ ያቀርባል። CLS ሕጋዊ ምክር በመስጠት፥ መልስና ሌሎች ሕጋዊ ሰነዶችን በማስገባት ወይም ፍርድ ቤት ውስጥ ጥብቅና በመቆም ሊረዳ ይችላል። ተከራይ ከሆኑና ማሳሰቢያ ከደረስዎት፥ የፍርድ ቤት ወረቀቶች ከደረስዎት ወይም የመኖሪያ ችግር ካለብዎት እባክዎን CLSን ወዲያውኑ ይገናኙ። | 303-837-1313<br><br>**coloradolegalservices.org** |
| **COLORADO AFFORDABLE LEGAL SERVICES (CALS) (የኮሎራዶ ተመጣጣኝ ዋጋ ሕጋዊ አገልግሎቶች)**<br><br>CALS አከራዮችና ተከራዮችን ሕጋዊ ጉዳዮችና ሌሎች የአከራይ/ተከራይ ጉዳዮች በተመለከተ ምክር ይሰጣል እንዲሁም ጥብቅና ይቆማል። በCALS ፍርድ ቤት ሂደቶች ላይ ሰዎች እንዴት ክስ እንደሚያስገቡ፥ እንደሚያስነሱና ራሳቸውን እንዴት እንደሚከላከሉ ምክር ይሰጣል፥ እንዲሁም ከርከር መፍቻ መረጃና ለሌሎች የሕግ ድጋፍ አገልግሎቶች ጥቆማ ከመስጠት በተጨማሪ የሽምግልና አገልግሎት ይሰጣል። | 303-996-0010<br><br>**coloradoaffordablelegal.com** |
| **COVI9-19 EVICTION DEFENSE PROJECT (የኮቪድ-19 ከመኖሪያ ማባረሪያ መከላከያ ፕሮጀክት)**<br><br>COVID-19 Eviction Defense Project የትብብር፥ ማህበረሰብ ላይ የተመሠረተ ፕሮጀክት ነው። ተልዕኮው በኮቪድ-19 ቀውስ ወቅት ኪራያቸውን መክፈል ላቃታቸው የኮሎራዶ ነዋሪዎች መረጃና ድጋፍ መስጠት ነው። | **cedproject.org** |
| **COLORADO COALITION FOR THE HOMELESS (በኮሎራዶ ለቤት አልባዎች ሕብረት)**<br><br>በኮቪድ-19 ቀውስ ወቅት በዴንቨር ውስጥ ቤት አልባነት ላጋጠማቸው ሰዎች የሞቴል/ሆቴል ክፍል በማቅረብ ድጋፍ ለመስጠት የዴንቨር ከተማና አውራጃ ከ Colorado Coalition for the Homeless እና ከ National Guard (ብሔራዊ ጥበቃ) ጋር አጋርነት ፈጥሯል። | 303-293-2217<br><br>**coloradocoalition.org/covid-19** |
| **DENVER SHERIFF DEPARTMENT CIVIL PROCESS OFFICE (የዴንቨር ፖሊስ መኮንን መምሪያ ሲቪል ሂደት ቢሮ)**<br><br>(የዴንቨር ፖሊስ መኮንን መምሪያ ሲቪል ክፍል) የሲቪል ሂደት የማቅረብ፥ በፍርድ ቤት ትእዛዝ መሠረት እውነተኛና የግል ንብረት የመሸጥ፥ በፍርድ ቤት የታዘዙ ማባረሮችን ማስፈጸምና ሌሎችም ኃላፊነቶች አለው። | 720-865-9556<br><br>201 W. Colfax Ave.<br>First Floor Atrium<br><br>**Denvergov.org/Sheriff** |
| **COLORADO HOUSING CONNECTS (የኮሎራዶ መኖሪያ ማገናኛ)**<br><br>Colorado Housing Connects አከራይ/ተከራይን የሚመለከቱ ጥያቄዎችና አሳሳቢ ጉዳዮችን በተመለከተ መረጃ ያቀርባል። | 1-844-926-6632<br><br>**coloradohousingconnects.org** |

| | |
|---|---|
| **NEIGHBORHOOD EQUITY AND STABILIZATION INITIATIVE (NEST) (የሰፈር እኩልነትና መረጋጋት መነሳሻ)**<br>የNEST ተልዕኮ ከፍተኛ ለውጥ ያጋጠማቸውን ሰፈርተኞች ድምጻቸውን ከፍ በማድረግ የማህበረሰባቸውን የወደፊት ሁኔታ ለመወሰን እንዲችሉ ለአቅም አነስ እና ለተገለሉ ነዋሪዎችና ንግዶች ድጋፍ መስጠት ነው። ራእያችን:- ቤት የመያዝ፥ ሥራ የመያዝና ወደፊቱን የመገንባት አቅምና ዕድል ያላቸው ንቁ፥ ፈጠራ ላይ የተሰማሩና የተገናኙ ማህበረሰቦች። NEST:<br>• የዘገየ የንብረት ግብር፥ ይዞታና ማገድ ለደረሰባቸው የቤት ባለቤቶች የማሳወቅና የድጋፍ የመድረስ ተግባር ያከናውናል<br>• መሠረታዊ ማህበረሰብ ማደራጀትን ይደግፋል<br>• ዝቅተኛና መካከለኛ ገቢ ላላቸው ግለሰቦች መርሃ ግብርና አገልግሎቶች ለሚያቀርቡ ለሠፈርና ለማህበረሰብ ድርጅቶች የገንዘብ ድጋፍ ያቀርባል። | **Denvergov.org/content/denvergov/en/denver-office-of-economic-development/housing-neighborhoods.html** |
| **DENVER REGIONAL COUNCIL OF GOVERNMENTS (DRCOG) AREA AGENCY ON AGING AND NETWORK OF CARE (ዴንቨር ክልላዊ የመንግሥት ምክር ቤት ያካባቢው የእርጅናና የእንክብካቤ አውታር ወኪል)**<br>DRCOG ለአዛውንቶችና ለተንከባካቢዎቻቸው ስለ አገልግሎቶች፥ ስለ ሕጋዊ ድጋፍና ስለ መኖሪያ ድጋፍን ጨምሮ ወቅታዊ መረጃ የሚያቀርብ ሁሉን አቀፍ፥ ማህበረሰብን መሠረት ያደረገ ድረገጽ አዘጋጅቷል። | **drcog.org/programs/area-agency-aging**<br>ዋና ስልክ ቁጥር:- 303-480-6700<br>የረጅም ጊዜ እንክብካቤ እንባ ጠባቂ:- 303-480-6734 |

ተጨማሪ በስቴት ደረጃ ያሉ መባረርን አስቀድሞ መከላከያ አገልግሎቶች በ **cdola.colorado.gov/housing-covid19-eviction** ይገኛሉ።